ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

# ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ
# አክሲዮኖችን በጨረታ ለመሸጥ የወጣ ማስታወቂያ

ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር FIS/01/2016 መሠረት የውጭ ሀገር ዜግነት ከያዙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለአክሲዮኖች የተረከባቸውን ብዛታቸው 69,929 የሆኑ አክሲዮኖች፣ የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 500.00 ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 34,964,500.00 የሚያወጡ አክሲዮኖችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም:-**

1. የአንድ አክሲዮን የጨረታ ወይም የመወዳደሪያ መነሻ ዋጋ ብር 600.00 (ብር ስድስት መቶ) ነው፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታው መግዛት የሚችሉት አነስተኛ የአክሲዮን ብዛት በቁጥር 200 በገንዘብ ደግሞ ብር 100,000.00 (ብር አንድ መቶ ሺ.ህ) ሲሆን ከዚህ በታች የሆኑ አክሲዮኖች ለመግዛት የሚቀርብ ተወዳዳሪ ከውድድሩ ውጪ ይሆናል፡፡
3. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ግለሰቦች ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለአክሲዮኖች የተያዙ ድርጅቶች በጨረታው መሳተፍና መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች መጫረት የሚፈልጉትን አክሲዮኖች ለዋጋ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ከጨረታው ቀን በፊት ቦሌ መንገድ ደንበል ህንፃ ላይ በሚገኘው 5ኛ ፎቅ በባንኩ ፋይናንስ እና አካውንትስ መምሪያ በመገኘት ሐምሌ 3 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የጨረታ ሠነዶችን በመውሰድ መሙላትና በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ እስከ ሐምሌ 17 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ በባንኩ 5ኛ ፎቅ በሚገኘው ፋይናንስ ኢንቨስትመንት እና አክሲዮን አስተዳደር ዋና ክፍል ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ጨረታው ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸውና ታዛቢዎች በተገኙበት ቦሌ መንገድ በሚገኘው አበሩስ ህንፃ 10ኛ ፎቅ የባንኩ የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል፡፡